## ድር ቢያድር አንበሳ

ተርተን፤ ተርተን፤  ስንተርረት ኖረናል፤
ግን ተረት ወግ ብቻ ልማድ ሆኖ ቀርቷል፤
ያበረው ድር እጃል እንዳው ለመሆኑ?
የሸረሪት ይሆን ወይስ የወይዘሮ?
ከጥጥ ውስጥ የወጣ በደጋን ተከሮ?

ያ የተፈተለው ድር እንዳይሆን እንጂ..
በሸረሪት ጥበብ በሸረሪት ደጂ;
እውነት ነው ትንኝም ዝምብም ቢሆን ሌላ፤
ጠፍሮ አስሮ ሲያቆይ ለዛች ባለመላ;
"አጅሬ ሸረሪት"
ለምን አትተርት!
ደር ቢአብር አያለች፤
ጠልፋ ለማስቀረት ጉልበት ስላገኘች!
ለሸረሪይቱ ብልጣብልጥ ፍጥረት፤
በራ በክንፎቿ በራሪ አትይዝበት!!

ስለዚህ ያበረው የሸረሪቱ ድር ፤
ወጥርኦ ይይዛል እጅ ወገብና እግር ፤
የተያዙት ደግሞ ከባድ ነው ለነሱ፤
በጥሶ ለመውጣት የግር ብረት ናሱ ፤
ስታመዛዝኑት ደርን ከሲል ነፍሳት ፤
ሰንሰለት ንው ከባድ የነጠረ በሳት ፤

የኛስ ደር ያበረው ለማሰር አክርሮ
ካላጣው እንሰሳ ተኩላና ቀበሮ
እያለ የከፋ ካንበሳ በምድር
አረ ለምን እንዴት አንበሳ ይታሰር?
 እውነት ካበረማ ያዛችሁት ድር
 ቀበሮን ነው ማሰር ተኩላን ማባረር;

አቦ ምን አረገ ? በጫካና በዱር
ከየመሰሉ ጋር ተጋጥሞ የሚኖር
አሸንፎ መሪ ግርማው የ አስፈራ
የውሬ የነፍሳት መሪ ነው አውራ!!

ግን እንዳው ተረቱ ትርጉም እንዳያጣ
ብሂል ምሳሌያችን በከንቱ እንዳልመጣ
ያባሪው ድር ጣጣ……
አንበሳን ለማሰር እውነት አቅም ካጣ፤
የምን ድር እንደሆን ከምን እንደመጣ
ተራቹ ያስረዳ ትንታኔ ያምጣ ::

ደረጀ አምስተርዳም ሜይ 2003

## ለፍፃሜህ ብቃ

አምኜ በየሱሰ እርሱ ሆኖ ክብሬ
የጅ የግር፤ ያንደት፤ያይምሮ፤ ውጣሬ፤
በመስቀሉ ስራ መርገሜን ቀብሬ፤

መሆን ሳይሆን ሆኖ ቀርቶ ከሚያንገበግበኝ
ሊሆን እንዲሳካ ማመንን መረጥኩኝ::

ካመን ዘንዳ ደግሞ ሁሉ እንዲሳካልን፤
አለቀ አከተመ፤ ሆኖ እናየዋለን;
ቅጥሩን እንዘላለን፤
አሜን ይሁንልን፤
አንተም ትዘላለህ አንቺም ታልፊዋለሽ!
አሜን በል እባክህ አሜን በይ በናትሽ!
ላንትም ይሁንልህ፤ላንቺም ይሳካልሽ፤
አሜን በይ ለየሱስ ቀኑ ሳይመሽብሽ፤
እሺ በሉ እናንተም ግዜው ሳይበላሽ፤

ደስ የማይል ዘመን ሳይመጣብህ ጭንቁ፤
ጨረቃ ከዋክብት ከሰማይ ሳይወድቁ፤
ታረቅ አሜን በለው ጥርጣሬህ ያብቃ፤
አንተም ለፍፃሜህ ለመድረሻህ ብቃ ::

ደረጀ

**Back to Meskot**

---

***The views reflected in the above poems are solely of the author and are not necessarily shared by** Meskot. **You may contact** Dereje  Mekuria  **at** drj_mekonen@yahoo.co.uk*